# እስላሞች በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የሚያነሷቸው ጥያቄዎች

1) ኢየሱስ ክርስቶስ ነቢይ ነው/መልእክተኛ ነው ለዚህ ማስረጃ ዮሐ.8፣42፣ ዮሐ.8፣40፣ ዮሐ.14፣24 ዮሐ.17፣14 ዮሐ.20፣17 ዮሐ.5፣19 ዮሐ.5፣30-32 ማቴ.15፣24

2) ምሥጢረ ሥላሴ ላይ ጌታ አንድም ሦስትም ሳይሆን ጌታ አንድ ነው ለዚህ ማስረጃ ማር.12፣29

3) ኢየሱስ ክርስቶስ አልተሰቀለም።(የመጽሐፍ ቅዱስ ግጭት በስቅለቱ ዙሪያ አለው ለዚህ ማስረጃ ማቴ.28፣3-7 ማር.16፣5-6 ሉቃ.4፣3-5 ዮሐ.20፣11-18)

4) በማቴዎስ ወንጌል 12፣29 ላይ ያለው አላህ አንድ ነው ከሚለው ጋር ይመሳሰላል?

## የጥያቄዎች መልስ

ከሁሉም በፊት መረዳት ያለብን ነገር ቢኖር የእግዚአብሔር ቃል አንድ ነው አይለወጥም። ነገር ግን በጥልቀት ለማያውቁት ሰዎች ነገሩ የተቃረነ ሊመስላቸው ይችላል። ስለዚህ ከእንደዚህ ዓይነት ችግር ለመዳን የመጽሐፍ ቅዱስ መምህራንን መጠየቅ አግባብ ነው። ምክንያቱም እንኳንስ መጽሐፍ ቅዱስ አንድ ምሳሌ ብናነሳ አንድን ዳገት ስንወጣው ዳገት እንለዋለን። ያንኑ ዳገት ግን ስንወርደው ቁልቁለት እንለዋለን። ቁልቁለት የዳገት ተቃራኒ ነው። ነገር ግን ዳገትም ቁልቁለትም የተባለ ያው አንዱ ቦታ ነው። ሁለቱም ደግሞ ትክክል ነው። ምክንያቱም ስንወርደው ቁልቁለት ስንወጣው ዳገት ነው። ይህ በእኛ በተለምዶ ያለ ነው። የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል እርስ በእርስ አይቃረንም። ምክንያቱም እግዚአብሔር አይለወጥም። መዝ.101፣27 ‹‹አንተ ግን ያው አንተ ነህ›› ተብሎ እንደተገለጠው ቃሉም አይለወጥም።ይህንን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ጥያቄዎችን ወደመመለስ እገባለሁ።

## ጥያቄ ቁጥር 1

አንደኛ ጥያቄ ዮሐ.8፣42 ‹‹እግዚአብሔር አባታችሁ ቢሆንስ እኔን በወደዳችሁኝ ነበር እኔ ከእግዚአብሔር ዘንድ መጥቻለሁና እኔ በገዛ እጄ የመጣሁ አይደለሁም እርሱ ላከኝ እንጂ›› የሚለው ነው።በመጀመሪያ ደረጃ ‹‹እግዚአብሔር›› በሚለው ቃል ኢየሱስ ክርስቶስም ይጠራል። ምክንያቱም ራሱ ኢየሱስ ክርስቶስም እግዚአብሔር ነውና።ለዚህ ከመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃ ላላችሁት ደግሞ ዮሐ.1፣1 ‹‹በመጀመሪያ ቃል ነበር።ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበር። ቃልም እግዚአብሔር ነበር›› ይልና ቁጥር 14 ላይ ‹‹ያም ቃል ሥጋ ሆነ በእኛም አደረ።ለአባቱ አንድ እንደሆነ ልጅ ክብር ያለ ክብሩን አየን›› ይላል። ስለዚህ ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ እግዚአብሔር ነው። እግዚአብሔር ከሆነ ከእግዚአብሔር ዘንድ መጥቻለሁ ለምን አለ ካላችሁ ደግሞ አስቀድሞ በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ ስለተባለ ከእርሱ ዘንድ የነበረው ቃል ወደእኛ መጣ ማለት ነው።እኔ በገዛ እጄ የመጣሁ አይደለሁም እርሱ ላከኝ እንጂ ያለው በፈቃድ አንድ ስለሆኑ እና በገዛ እጄ አልመጣሁም ያለው ደግሞ ከአብ የተለየ ስላልሆነ ነው። ምክንያቱም በአብ ያለ ከአብ ያልተለየ ለመሆኑ ማስረጃ ደግሞ ይሄው በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ ያለው

ቃል ነው። ‹‹ላከኝ›› ያለው ቃል ደግሞ ወልድ ሰው ለመሆን መላኩን ያመለክታል። ምክንያቱም ሰው የሆነ ወልድ እንጂ አብ አይደለም።ስለዚህ ተላከ የሚባል በተለየ ወልድ ነው። ነገር ግን መላክ የሚለው ቃል ማነስና መብለጥን አያመለክትም። በወልድ መላክ ውስጥ የወልድም የአብም ፈቃድ አንድ ነው።ለዚህም ማስረጃችን ዮሐ.10፣30 ‹‹እኔ እና አብ አንድ ነን›› ብሏልና ነው።ማቴ.15፣24ም ትርጉሙ ከዚህ ጋር ተመሳሳይ ነው።

**ሁለተኛው ጥያቄ** ዮሐ.8፣40 ‹‹አሁንም በእግዚአብሔር ዘንድ የሰማሁትን እውነት የምነግራችሁን ሰው ልትገድሉኝ ትሻላችሁ››።ይህም ምንም አሻሚ ነገር የለውም። እግዚአብሔር ሰው እንደሆነ ቀድመን ዮሐ.1፣14 ላይ ተናግረናል። ሰው ስለሆነ በሰውነቱ ሊገድሉት ይፈልጉ ነበርና ልትገድሉኝ ትሻላችሁ ብሏቸዋል።በእግዚአብሔር ዘንድ የሰማሁትን ያለው ደግሞ ወልድ ራሱ በአብ ያለ አብም በወልድ በህልውና ስላለ ነው። ወልድ በአብ ስላለ በአብ ያለውን ይሰማል ያውቃል።ዮሐ.14፣10 ‹‹እኔ በአብ እንዳለሁ አብም በእኔ እንዳለ አታምንምን?››የሚለው ቃል ይህንን ያረጋግጥልናል።

**ሦስተኛው ጥያቄ** ዮሐ.14፣24 ‹‹የማይወደኝ ግን ቃሌን አይጠብቅም።ይህም የምትሰሙት ቃል የላከኝ የአብ ቃል ነው እንጂ የእኔ ቃል አይደለም››።ይህንን ቃል በጥንቃቄ ተመልከተው።መጀመሪያ ‹‹የማይወደኝ ግን ቃሌን አይጠብቅም›› የሚለውን እንይ።ከዚህ ላይ ‹ቃሌ› በማለት ቃሉ የራሱ መሆኑን አስረግጦ ነግሮናል። ቀጥሎ ደግሞ ‹‹ይህም የምትሰሙት ቃል የላከኝ የአብ ቃል ነው›› የሚለውን እንይ ዮሐ.17፣10 ላይ ‹‹የእኔም የሆነ ሁሉ የአንተ ነው የአንተም የሆነ ሁሉ የእኔ ነው›› ብሎ ቀጥሎ ስለሚያመጣው የወልድ የሆነ ሁሉ የአብ የአብ የሆነ ሁሉ የወልድ ስለሆነ ከላይ ወልድ ቃሌ ያለውን ከዚህ ደግሞ የአብ ቃል አለው።ስለዚህ ምንም የሚጋጭ ነገር የለውም። ከዚያ ቀጥሎ ‹‹እንጂ የእኔ ቃል አይደለም›› የሚለው ነው።ይህ የሚያመለክተን ወልድ ከአብ የተለየ ቃል እንደሌለው ነው። ምክንያቱም የወልድ ቃል ብቻ ቢሆን ኖሮማ ቃሌ ያለውን የአብ ቃል ነው አይለውም ነበር። ስለዚህ እንጂ የእኔ ቃል አይደለም ያለው የእኔ የተለየ ቃል አይደለም ማለት ነው። የወልድ ለአብ የሌለው ቃል ለአብም ለወልድ የሌለው ቃል የለውምና ነው።ወልድ በዮሐ.16፣15 ‹‹ለአብ ያለው ሁሉ የእኔ ነው›› ተብሏልና። የአብ ብቻ እንዳንል ‹‹ለአብ ያለው ሁሉ›› ብሎ ሁሉ ስላለ የወልድ የሌለው የአብ ያለው ቃል እንደሌለ ያስረግጥልናል።

**አራተኛው ጥያቄ** ዮሐ.17፣14‹‹እኔ ቃልህን ሰጠኋቸው››።ሰው ሆኖ ሥጋ ለብሶ በሰው ቋንቋ ያስተማረ በተለየ አካሉ ወልድ ነው። አብ ወደዚህ ምድር መጥቶ አላስተማረም። በተለየ መጥቶ ያስተማረ እግዚአብሔር ወልድ ነው። የእግዚአብሔር ወልድ ቃል እና የእግዚአብሔር አብ ቃል ደግሞ አንድ እንደሆነ ከላይ ዮሐ.17፣10 አይተናል። ስለዚህ ቃልህን ሰጠኋቸው ቢል ምንም ግራ የሚያጋባ ነገር የለውም። የአብም የወልድም አንድ ቃል ነው ያላቸው።ያንኑ አንድ ቃል ለአብ ቃልህ ቢለው ራሱ ወልድ ደግሞ ቃሌ ቢለው አይለያይም። ይህ ደግሞ ለምሳሌ የእኔም የአንተም አንድ ሀገር ቢኖረን እኔም ‹ሀገሬ ኢትዮጵያ› ብል አንተም ‹ሀገሬ ኢትዮጵያ› ብትል አንድ ሀገር እስካለን ድረስ ሁለቱም ያስኬዳል አያይገፍ ‹ሀገርህ ኢትዮጵያ ናት› ብልህ የእኔ ሀገር ኢትዮጵያ አይደለችም እያልከህ እንዳልሆነ ግልጥ ነው። እንዳው በምሳሌ ላስረዳህ ብየ ነው።አብም ወልድም አንድ ቃል እስካላቸው ድረስ አብም ቃሌ

ቢል ወልድም ቃሌ ቢል አንድ ነው።ወልድ አብን ቃልህን ሰጠኋቸው ቢለው። ራሱ ወልድም ሌላ ቦታ የማይወደኝ ግን ቃሌን አይጠብቅም ቢል አንድ ነው።

**አምስተኛ ጥያቄ** ዮሐ.20፣17 ‹‹ወደ አባቴ ወደ አባታችሁ ወደ አምላኬ ወደ አምላካችሁ አርጋለሁ››።በዚህ ቃል የምናስተውላቸው ቃላት አሉ።ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክም ሰውም ለመሆኑ በቂ ማስረጃ የሚሰጠን ቃል ይህ ነው።ክርስቶስ ነቢይ እና መልእክተኛ ሰው ብቻ /ዕሩቅ ብእሲ/ ቢሆን ኖሮ ማለት የነበረበት ‹‹ወደ አባታችን ወደ አምላካችን አርጋለሁ›› ባለ ነበር።ነገር ግን አምላክ የሆነ ሰው ሰው የሆነ አምላክ መሆኑን አስረግጦ ለማሳየት ‹‹ወደ አባቴ ወደ አባታችሁ ወደ አምላኬ ወደ አምላካችሁ›› ብሎ ለይቶ ተናገረ። ለምን አባቴ አለ ካልን ወልድ የአብ የባሕርይ ልጅ ስለሆነ ነው። የእግዚአብሔር ልጅ እግዚአብሔር ስለሆነ ነው። ማቴ.3፣17 ‹‹በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው›› ተብሎም በሌላ አንቀጽ ተገልጧል። ማቴ.17፣5፤ ማር.1፣10፤ ማር.9፣7፤ ሉቃ.3፣22፤ ሉቃ.9፣35። ስለዚህ ለይቶ አባቴ አለ። አባታችሁ ያለ ደግሞ ለምእመናን በጸጋ አባታቸው ስለሆነ ነው። አስተውል ወልድን የእግዚአብሔር ልጅ ስንለው የእግዚአብሔር ልጅ እግዚአብሔር ነው። ሰውን ግን የእግዚአብሔር ልጅ ስንለው የጸጋ ስለሆነ የእግዚአብሔር ልጅ ሰው እንላለን እንጂ የእግዚአብሔር ልጅ እግዚአብሔር አንለውም።ለዚህ ማስረጃ የሚሆነን ማቴ.6፣9 ‹‹እናንተስ በምትጸልዩበት ጊዜ እንዲህ በሉ አባታችን ሆይ በሰማያት የምትኖር ስምህ ይቀደስ...›› የሚለው ነው። በዚህ ጊዜ አባታችን ሆይ በሉ ብሎ አስተምሮ ነበርና አባታችሁ ያለ ለዚያ ነው።አብ ለወልድ አባቱ ሲባልና አብ ለሰው አባቱ ሲባል የተለያየ መሆኑን ከላይ በገለጥኩልህ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል አስተውል። ወደ አምላኬ ወደ አምላካችሁ ያለውን ደግሞ ቀጥለን እንመልከት። ዮሐ.1፣14 ላይ ቃል ሥጋ ሆነ ብለን ነበር።ቃል እግዚአብሔር ነው። ይህ እግዚአብሔር ደግሞ ሰው ሆነ ካልን እንዴት ነው ሰው የሆነ የሚል ጥያቄን ያስከትላል።ክርስቶስ ራሱ የፈጠረውን ሥጋ ነው የተዋሐደው። እንዴት ከተባለ ሰው በእግዚአብሔር የተፈጠረ እንደሆነ ዘፍ.2፣7 ‹‹እግዚአብሔር አምላክም ሰውን ከምድር አፈር ፈጠረው›› ተብሎ ተገልጧል። አምላካችሁ ያለ ይህን ይዞ ነው። ፍጥረት ሁሉ የተፈጠረው በእግዚአብሔር ነው ማለት ነው።ዮሐ.1፣3 ‹‹ሁሉም በእርሱ ሆነ ከሆነውም ሁሉ ያለእርሱ ምንም የሆነ የለም›› ተብሏል።እንዲህ የተባለ ደግሞ ቃል እግዚአብሔር ነው። ስለዚህ ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ ለመሆኑ ምንም ጥርጥር የለውም።ሮሜ.5፣9 ‹‹ከእነርሱም ክርስቶስ በሥጋ ተወለደ እርሱም ከሁሉ በላይ የሆነ የዘለዓለም ቡሩክ አምላክ ነው›› ተብሎም የዘለዓለም አምላክ ለመሆኑ ተነግሯል።እንዲህ ከሆነ አምላኬ ለምን አለ ከተባለ።የተዋሐደውን ሥጋ የፈጠረ ስለሆነ ነው።ክርስቶስ ሰው የሆነ አምላክ ነው የምንለውም ለዚህ ነው። ቃል ሥጋ ሲሆን ቃልነቱን ወይም እግዚአብሔርነቱን ትቶ ወይም ተለውጦ አይደለም።እንዳልተወ የሚያስረዳን ራሱ ኢየሱስ ክርስቶስ በዮሐ.8፣58 ‹‹አብርሃም ሳይወለድ እኔ አለሁ›› ያለው ቃሉ ነው። በማቴ.1፣1 ‹‹የዳዊት ልጅ የአብርሃም ልጅ የኢየሱስ ክርስቶስ ትውልድ መጽሐፍ› ይላል። ከአብርሃም በፊት ከነበረ ለምን ከዚህ ደግሞ የአብርሃም ልጅ አለው ከተባለ ከአብርሃም በፊት እንደ አምላክነቱ ነበረ። ከአብርሃም ደግሞ በሥጋ ተወለደ። ይህንን ሥጋ የፈጠረ ስለሆነ አምላኬ አለው። በአምላክነቱ ግን እንዳልፈጠረው ደግሞ ያለ እርሱ ምንም ምን የሆነ የለም ብሎ ገለጠው ዮሐ.1፣3። ስለዚህ ይህም ጥቅስ የተዋሐደውን ሥጋ እግዚአብሔር እንደፈጠረው የሚናገር እንጂ ኢየሱስ ክርስቶስ

ፍጡር ብቻ እንደሆነ ወይም ነቢይ እና መልእክተኛ እንደሆነ አይናገርም። ነቢይ ወይም መልእክተኛ ሆኖስ ቢሆን ኖሮ አብርሃም ሳይወለድ እኔ ነበርኩ ባላለ ነበር።

**ስድስተኛ ጥያቄ ዮሐ.5፣19** ‹‹እውነት እውነት እላችኋለሁ ወልድ ከራሱ ብቻ ምንም ሊያደርግ አይችልም አብ ሲያደርግ ያየውን ነው እንጂ››።ወልድ ከራሱ ብቻ ምንም ሊያደርግ አይችልም ያለው እውነት ነው።ምክንያቱም መጀመሪያውንም ወልድ የራሱ ብቻ የሆነ ነገር የለውም።በዮሐ.17፣10 ላይ የእኔ የሆነው ሁሉ የአንተ ነው።የአንተ የሆነው ሁሉ የእኔ ነው ብሎ ግልጽ አድርጎ አስቀምጦልናል። የአብ የሆነው ሁሉ የወልድ ከሆነ የወልድ የሆነው ሁሉ የአብ ከሆነ የወልድ ብቻ የሚባል ነገር የለም ማለት ነው። እንዲሁ የአብ ብቻ የሚባል ነገርም የለም ማለት ነው። ምክንያቱም የአብ የሆነው ሁሉ የወልድ ነውና። ይህ ከላይም በደንብ ስለተብራራ ያንንም ማየት ነው።

**ሰባተኛ ጥያቄ ዮሐ.5፣30-32** ‹‹እኔ ከራሴ አንዳች አደርግ ዘንድ አልችልም።እንደሰማሁ እፈርዳለሁ እንጂ ፍርዴም እውነት ነው የላከኝን ፈቃድ እንጂ የእኔን ፈቃድ አልሻምና።እኔ ለራሴ ብመሰክር ምስክርነቱ እውነት አይደለም።ነገር ግን ለእኔ የሚመሰክር ሌላ ነው ስለእኔ የሚመሰክረው ምስክርነቱም እውነት እንደሆነ አውቃለሁ›› የሚለው ነው።ይህም ጥቅስ ኢየሱስ ክርስቶስ ነቢይ ወይም መልእክተኛ እንደሆነ የሚያመለክት ምንም ነገር የለውም።እኔ ለራሴ ብመሰክር ምስክርነቱ እውነት አይደለም ያለው ማቴ.11፣29 ‹‹ከእኔም ተማሩ እኔ የዋሕ በልቤም ትሑት ነኝና›› ብሎ እንደነገረን ራሳችሁ ለራሳችሁ አትመስክሩ ሌላ ይመስክርላችሁ ለማለት ትሕትናን ለማስተማር የተናገረው ቃል ነው። የሰው ልጅ ራሱ ለራሱ መመስከር አይገባውምና ቢመሰክርም ምስክርነቱ እውነት ተደርጎ ተቀባይ አይሆንም ሌላ ሰው ሊመሰክርለት ይገባል።ያንን ልማድ ነው ክርስቶስ የተናገረው። እንጂ ክርስቶስ የሚናገረው ነገር ሁሉ እውነት እንደሆነማ ዮሐ.8፣14 ‹‹ኢየሱስም መልሶ አላቸው እኔ ስለራሴ ምንም እንኳ ብመሰክር ከወዴት እንደመጣሁ ወዴትም እንድሄድ አውቃለሁ ምስክርነቱ እውነት ነው›› ብሎ በግልጽ ቋንቋ ነግሮናል።የላከኝን ፈቃድ እንጂ የእኔን ፈቃድ አልሻም ያለውም ፈቃዳቸው አንድ ስለሆነ የተነገረ ቃል ነው።ዮሐ.10፣30 ‹‹እኔና አብ አንድ ነን›› ብሎ ተናግሯልና።የእኔን ፈቃድ አልሻም ማለቱ መጀመሪያውንም የራሱ ብቻ ፈቃድ እንደሌለው የሚያሳስብ ቃል ነው።

## ጥያቄ ቁጥር 2

ማር.12፣29 ‹‹ከትዕዛዛቱ ሁሉ የምትበልጠው ይች ናት።እስራኤል ሆይ ስማ እግዚአብሔር አምላካችን አንድ እግዚአብሔር ነው››።በነገራችን የክርስትና ሃይማኖት የምናምነው እምነትም ይህ ነው። እግዚአብሔር አምላካችን አንድ ነው።ሁለት አምላክ፣ሦስት አምላክ፣ አራት አምላክ የለንም።አምላካችን አንድ እግዚአብሔር ነው።ይህ አንዱ እግዚአብሔር ግን ሦስት አካል አለው ነው ያልን።ለዚህ ደግሞ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃው ዮሐ.1፣1 ነው። ‹‹በመጀመሪያ ቃል ነበር። ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበር። ቃልም እግዚአብሔር ነበር። ይህም በመጀመሪያ በእግዚአብሔር ዘንድ ነበር›› የሚለው ቃል ነው። ይህ ቃል ሦስት አካላት አንድ እግዚአብሔር እንዳለ የሚያመለክተን ቃል ነው።ቃል በእግዚአብሔር ዘንድ ነበር ብሎ አንድ፣ ቃልም

እግዚአብሔር ነበር ብሎ ሁለት፣ ይህም በመጀመሪያ በእግዚአብሔር ዘንድ ነበር ብሎ ሦስት አካላትን ጠቅሷል። ሦስት አካል ስላልን ግን ሦስት አምላክ አንልም። አንዱ እግዚአብሔር ሦስት አካል አለው እንላለን እንጂ።ቃሉ ራሱ አካል ያለው እግዚአብሔር ነው።እስትንፋሱ ራሱ አካል ያለው እግዚአብሔር ነው።ማቴ.28፣19-20 ‹‹እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስቅዱስ ሥም እያጠመቃችኋቸው ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀመዛሙርት አድርጓቸው›› ተብሎ በመገለጥ የእያንዳንዱን አካላት ሥም ገልጦልናል።ሉቃ.10፣22 ‹‹ወልድንም ማን እንደሆነ ከአብ በቀር የሚያውቅ የለም›› ብሎ የአብና የወልድን ሥም ጠቅሷል።ዮሐ.15፣16 ‹‹ዳሩ ግን እኔ ከአብ ዘንድ የምልክላችሁ አጽናኝ እሱም ከአብ የሚወጣ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ እርሱ ስለእኔ ይመሰክራል›› ተብሎ ምሥጢረ ሥላሴ በተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ተገልጧል።

## ጥያቄ ቁጥር 3

መጀመሪያ ተቃርነዋል ያላችኋቸውን ጥቅሶች ሙሉውን ልጻፋቸው።በነገራችን ላይ የራሳችሁ የአረዳድ ችግር ካልሆነ በስተቀር ምንም እርስ በእርሱ የተቃረነ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል የለም። ማቴ.28፣3-7 ‹‹ልብሱም እንደበረዶ ነጭ ሆነ እርሱንም ከመፍራት የተነሳ መቃብሩን የሚጠብቁ ታወኩ።እንደ በድንም ሆኑ።መልአኩም መልሶ ሴቶችን እንዲህ አላቸው እናንተስ አትፍሩ የተሰቀለውን ኢየሱስን እንደምትሹ አውቃለሁና በዚህ የለም እርሱ እንደተናገረው ተነስቷልና።ነገር ግን ኑና ተቀብሮበት የነበረውን ቦታ እዩ ፈጥናችሁም ሂዱና ከሙታን ተለይቶ ተነሳ እነሆ ወደ ገሊላ ይቀድማችኋል። በዚያም ታዩታላችሁ ብላችሁ ለደቀመዛሙርት ንግሯቸው›› ማር.16፣5-6 ‹‹ወደመቃብሩም በገቡ ጊዜ አንድ ጎልማሳ ነጭ ልብስ ለብሶ በስተቀኝ ተቀምጦ አገኙና ደነገጡ።እርሱም እንዲህ አላቸው አትደንግጡ የተሰቀለውን የናዝሬቱን ኢየሱስን ትሻላችሁን ተነስቷል።በዚህስ የለም የተቀበረበትም ቦታ እነሆ››።ሉቃ.24፣3-5 ‹‹ገብተውም የጌታችን የኢየሱስን ሥጋ አላገኙም ስለዚህም ነገር የሚሉትን አጥተው ሲያደንቁ ሁለት ሰዎች በፊታቸው ቆመው ታዩዋቸው ልብሳቸውም ያብረቀርቅ ነበር።ፈርተውም ፊታቸውን ወደምድር አቀረቀሩ እነርሱም እንዲህ አሏቸው ሕያውን ከሙታን ጋር ለምን ትሹታላችሁ በዚህ የለም ተነስቷል›› ዮሐ.20፣11-18 ‹‹ማርያም ግን ከመቃብሩ በስተውጭ እያለቀሰች ቆማ ነበር።እያለቀሰችም ወደ መቃብር ጎንበስ ብላ ተመለከተች።ሁለት መላእክትንም ነጭ ልብስ ለብሰው የጌታችን የኢየሱስ ሥጋ በነበረበት ቦታ አንዱ በራስጌ አንዱም በግርጌ ተቀምጠው አየች።እነዚያ መላእክትም አንቺ ሴት ምን ያስለቅስሻል አሏት።እርሷም ጌታየን ከመቃብር ውስጥ ወስደውታል።ወዴትም እንደወሰዱት አላውቅም አለቻቸው።ይህንንም ተናግራ ወደኋላዋ መለስ ስትል ጌታችን ኢየሱስን ቆሞ አየችው ጌታችን ኢየሱስም እንደሆነ አላወቀችም ጌታችን ኢየሱስም አንቺ ሴት ምን ያስለቅስሻል ማንንስ ትሻለሽ አላት እርሷ ግን የአትክልት ቦታ ጠባቂ መስሏት ጌታዬ አንተ ወስደኸው እንደሆነ ዜጂ ወደእኔ እንዳመጣውና ሸቱ እንድቀባው ወዴት እንዳኖርኸው ንገረኝ አለችው።ጌታችን ኢየሱስም ማርያም አላት።እርስዋም መለስ ብላ በዕብራይስጥ ቋንቋ ረቡኒ አለችው ትርጓሜውም መምህር ማለት ነው።ጌታችን ኢየሱስም አትንኪኝ ገና ወደ አባቴ አላረግሁምና ነገር ግን ወደ ወንድሞቼ ሂጂና ወደ አባቴ ወደ አባታችሁ ወደ አምላኬ ወደ አምላካችሁ አርጋለሁ አለ ብለሽ ንገሪያቸው አላት።ማርያም

መግደላዊትም ሄደች ጌታን እንደአየች ይህንም እንዳላት ለደቀመዛሙርቱ ነገረቻቸው››።በትንሳኤ የተደረገውን ድርጊት አራቱ ወንጌላውያን ተካፍለው ጽፈውታል።እንደ ወንጌላዊው ቅዱስ ማቴዎስ አጻጻፍ በአንድ ወገን የመጡ ብዙ ሴቶች በውጭ አንድ መልአክ አይተው ሲመለሱ እንደ ወንጌላዊው ቅዱስ ማርቆስ በአንድ ወገን የሄዱ ብዙ ሴቶች አንድ መልአክ በውስጥ አዩ አለ።ወንጌላዊው ቅዱስ ሉቃስ ቦታ ሳይለይ ብዙ ሴቶች ሁለት መላእክት አለ።ወንጌላዊው ቅዱስ ዮሐንስ አንዲት ሴት አለ።ለመንገር ከበቃች ብሎ። ስለዚህ አንዱ ያልጻፈውን አንዱ እየጻፈው ተካፍለው ጽፈውታል እንጂ ከጻፉት እርስ በእርሱ የሚቃረን አንድም ቃል የለም።ተካፍሎ መጻፍ ማለትም ለምሳሌ ስለአንድ ረጅም ቀይ ሰው ሁለት ሰዎች ቢጽፉ አንዱ ቀይ ነው ቢል ሁለተኛው ደግሞ ረዥም ነው ቢል ሁለቱም ትክክል ናቸው።ሁሉም በተረዱት መልኩ ገልጸውታልና። የመጽሐፍ ቅዱስ ቃልንም ያጻፋቸው አንድ መንፈስ ቅዱስ ስለሆነ ቃሉ የተነገረበትን ዓውድ ላልተረዳ ሰው የተለያየ ሊመስለው ይችላል እንጂ ልዩነት የለበትም።

## ጥያቄ ቁጥር 4

ማቴ.12፣29 ‹‹እኔ በእግዚአብሔር መንፈስ አጋንንትን የማወጣ ከሆንሁ ግን እንግዲያስ የእግዚአብሔር መንግሥት አሁን ወደ እናንተ ደርሳለች።ኃይለኛንም አስቀድሞ ካላሰረ በቀር ወደ ኃይለኛ ቤት ለመግባት ገንዘቡንም ለመበርበር የሚችል ማንም የለም ከዚህም በኋላ ቤቱን ይመረምራል›› ይላል።ይህ ቃል አላህ አንድ ነው ከሚለው ጋር ይመሳሰላል ላልከው ምኑ እንደተመሳሰለብህ ገርሞኛል።ምኑም አይመሳሰልም። እግዚአብሔር ሌላ ነው።አላህ የምትለውም ሌላ ነው። አላህ መሐመድ በምናቡ የፈጠረው ምናልባትም ከ7ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ የተፈጠረ ምናባዊ አምላክ ነው። እግዚአብሔር ግን አስቀድሞ ለአዳም የተገለጠ በኋላ ለሙሴ ተገልጦ ኦሪትን የሰጠ፣ ለነቢያት ትንቢትን ያናገረ እንደገና ከድንግል ማርያም ተወልዶ ሐዋርያትን ያስተማረ ፍጥረታትን ሁሉ የፈጠረ አምላክ ነው። እንጂ በ7ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ከመጽሐፍ ቅዱስም ከሌሎች መጻሕፍትም ገልብጦ ጽፎ ቁርዓን ከአላህ ወረደልኝ እንዳለው መሐመድ አይደለም። እግዚአብሔር ሌላ ነው። አላህ ሌላ ነው። ቁርአን ላይ የእነ አብርሃም የእነ ኖኅ ታሪክ አለ።ምክንያቱም መሐመድ እና ተከታዮቹ ከመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኩን እየወሰዱ ስለገለበጡት ነው። ይህ ደግሞ ኩረጃ /plagiarism/ ነው።እና የማይመሳሰል ነገርን ለማመሳሰል መጣር ትልቅ ነውር ነው።


መምህር በትረማርያም አበባው

የመጻሕፍተ ብሉያትና የመጻሕፍተ መነኮሳት ትርጓሜ መምህር

እንዲሁም አሁን የ3ኛ ዓመት የመጻሕፍተ ሊቃውንት ደቀመዝሙር

ሚያዝያ ፲፪ ፳፻፲፬ ዓ.ም

ኢትዮጵያ